ሁሉም አልተጓተቱም

ብ. ነጋሽ

የበለጸጉት የአውሮፓ አገራትና ሰሜን አሜሪካ የእድገት ጉዟቸውን የጀመሩት በ17ኛው ክፍለ ዘመን ነው ። 17ኛው ክፍለ ዘመን ከፊውዳሊዝም ወደካፒታሊዝም የተሸጋገሩበት የኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን ነበር። በተለይ የእንፋሎት ሞተር መስራት ግዙፍ ፋብሪካዎችን ለማቋቋምና ከፍተኛ መጠን ያለው የኤሌትሪክ ሃይል ለማመንጨት ያስቻለ ሁኔታ ፈጥሯል። የመጀመሪያዎቹ ሃዲድ ነክሶ አገር የሚያቋርጥ ባለሞተር ባቡርና ውቅያኖስ ሰንጥቆ አህጉራትን የሚያገናኝ ባለሞተር መርከብ የእንፋሎት ሞተር ውጤቶች ናቸው። ከአውሮፓ ውጭ ያሉት አሁን የብልጽግና ማማ ላይ በመውጣት ላይ የሚገኙት የደቡብ ምስራቅ ኢሲያ መሰላሉን አንድ ብለው የጨበጡት አብዛኞቹ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነው። እርግጥ ጃፓን የሃያኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ የፈጣን እድገት ጉዞ ጀመረች። የተቀሩት የኢሲያ አገራትና አፍሪካ፤ እንዲሁም የተወሰኑ የደቡብ አሜሪካ ሃገራት ግን የድህነትን ጨለማ ማሸነፍ ሳይችሉ ቀርተዋል። ጨለማዋ አህጉር ስትባል የኖረችው አፍሪካ አሁን አሁን ጥቅጥቁን የድህነት ጭለማ ለመግፈፍ ተስፋ ሰጪ ጥረት ማድረግ ጀምራለች። ጥቅጥቁን የድህነት ጨለማ ለመገፈፍ ጥረት ከሚያደርጉት የአፍሪካ ሃገራት መሃከል ኢትዮጵያ በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱት አንዷ ነች።

ኢትዮጵያ ከክርስቶስ ለደት በፊት ጀምሮ በወቅቱ ከነበረችበት የብልጽግና ማማ ላይ ቁልቁል ስትንሸራተት ኖራለች። ባለፉት ሁለት አስርት አመታት ግን ይህ የቁልቁለት ጉዞ በቃኝ ብላለች። አሁን ሽቅብ ጉዞ ጀምራለች። ኢትዮጵያን የሚመለከቱ ዓለም አቀፍ ዜናዎች በረሃብ ምክንያት ስለተፈጠረ እልቂት፣ በሽታ፣ የህጻናት ሞት፣ የትምህርት እጦት፣ የእርስ በርስ ጦርነት ወዘተ. መሆኑ ካበቃ ከራርሟል። ኢትዮጵያ አሁን የሚነገሩ በርካታ ስኬቶች እያስመዘገበች ያለች ሃገር ነች።

ኢትዮጵያ በንጹህ መጠጥ ወሃ አቅርቦት፣ በእናቶችና ህጻናት ሞት ቅነሳ፣ በአገር ደረጃ በምግብ ራስን በመቻል፣ ድህነትን በመቀነስ ወዘተ. እ ኤ አ ከ2000 እስከ 2015 ዓ.ም ተግባራዊ የተደረገውን የተባበሩት መንግስታት የሚሊኒየም የልማት ግቦች በማሳካት እውቅና አግኝታለች። የኤሌትሪክ ሃይል በማመንጨት እና ቀጠናዊ የሃይል ትስስር ለመፍጠር በያዘችው እቅድና ባከናወነቻቻው ተገባራት ትጠቀሳለች። በተተራመሰው የምስራቅ አፍሪካ ቀጠና የሰላም ደሴት ስለመሆኗ፣ የቀጠናውን ሰላም ለማስጠበቅ ስለምታደርገው ጥረት ይወራላታል። ድርቅ ችጋር አስከትሎ ዜጎቿን እንደቅጠል የሚያረግፍበትን የታሪክ ምእራፍ በመዝጋታ ትጠቀሳለች፤ በኢትዮጵያ አሁን ድርቅና ችጋር ተለያይተዋል። ኢትዮጵያ አሁን ከ95 በመቶ በላይ ህጻናቷ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት እድል አግኘተዋል። ግማሽ ያህሉ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አግኝተዋል። 1350 ያህል በሚሆኑ በመለስተኛ ባለሞያነት በሚያሰለጥኑ የሞያና ቴክኒክ ተቋማት፣ በሚሊየን የሚቀጠሩ ወጣቶች የስልጠና እድል አግኝተዋል። ከ33 በላይ በሚሆኑት ዩኒቨርሲቲዎቿ በሚሊየን የሚቆጠሩ ከፍተኛ ባለሞያዎችን ማስተማር የምትችልበት ደረጃ ላይ ደርሳለች። ከሃያ አምስት አመታት በፊት እነዚህ ስኬቶች ይደረስባቸዋል ተብለው የሚታሰቡ አለነበሩም።

ኢትዮጵያ ባለፉት አስራ አራት አመታት ባለሁለት አሃዝ የኢኮኖሚ እድገት አስመዝግባለች። በ2007 በተከሰተው ከፍተኛ ድርቅ ምክንያት ይህ እድገት በ2008 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደአንድ አሃዝ ወርዶ 8 በመቶ ሆኗል። 8 በመቶ የኢኮኖሚ እድገት ግን ብዙ አገሮች ተመኝተው ያላሳኩት ነው። ከ5 በመቶ አማካይ የአፍሪካ እድገት ጋር ሲነጻጸርም ከፍተኛ እድገት የሚባል ነው። በአጠቃላይ ከ7 በመቶ በላይ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ነው።

መንግስት በአገሪቱ ለተመዘገቡ ያለፉት ዓመታት የኢኮኖሚ እድገት ለቀጣይ እድገትም የተመቻቸ ሁኔታ እንዲፈጠረር አድርጓል። ቀዳሚው አመቺ ሁኔታ ምቹ የኢንቨስተመንት ፖሊሲ ሲሆን ሌላው ለግዙፍ የመሰረተ ልማት ግንባታ ትኩረት መሰጠቱ ነው። ልዩ ተኩረት ከተሰጣቸውና ለኢኮኖሚው እድገት ወሳኝ ከሆኑት ግዙፍ የመሰረተ ልማት ግንባታዎች መሃከል መንገድ፣ ሃይል፣ ቴሌኮም፣ ባቡር፣ የመስኖና የመጠጥ ወሃ አቅርቦት የመሳሰሉ ግንባታዎች ተጠቃሽ ናቸው። በእነዚህ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ግንባታ ትልቅ ስኬት ተመዝግቧል። በአሁኑ ወቅትም በርካታ ግንባታዎች በመከናወን ላይ ይገኛሉ። ለማስታወስ ያህል የተወሰኑትን እንመልከት።

በመንገድ ለማት ዘርፍ፣ ከደርግ መውደቅ በኋላ ባሉት አምስት ዓመታት መንግስት በመንገድ መለሶ ግንባታ ፕሮግራም በጦርነት የተጎዱ መነገዶችን ከመጠገን ጎን ለጎን አዳዲስ የአሰፋልት፣ የጠጠርና የገጠር የበጋ መነገዶች ግንባታን በማከናወን ነበር የመንገድ ዘርፍ መሰረተ ልማት የማስፋፋቱን ስራ የጀመረው። ከዚያ በኋላ በ1989 ዓ/ም የመንገድ ልማት ፕሮግራሞች ተቀርጸው ተግባራዊ ተደረገዋል። በዚህም ወደ 1 መቶ ሺህ ኪሎ ሜትር የሚጠጋ መነገድ ተገንብቷል። በ1983 ዓ/ም 19 ሺህ 17 ኪሎ ሜትር ብቻ የነበረው የሃገሪቱ መነገድ በ2003 ዓ/ም ወደ 110 ሺህ 414 ኪሎ ሜትር አድጓል። ልብ በሉ፣ ሃያ አመት በማይሞላ ግዜ የሃገሪቱ የመንገድ አቅም በ6 እጥፍ ገደማ ነው ያደገው።

የኤሌትሪክ ሃይል መሰረተ ልማት ላይም ተመሳሳይ ድንቅ ስኬት ነው የተመዘገበው። ሃገሪቱ ከኤሌትሪክ ሃይል ጋር ከተዋወቀችበት ከ1920ዎቹ አጋማሽ ጀምሮ እስከ 1983 ዓ/ም ባሉት 60 ዓመታት እደሜ አጠቃላይ በሃገሪቱ ይመነጭ የነበረው ሃይል 350 ሜጋ ዋት ብቻ ነበር።

የኢትዮጵያ መንግስት ከደርግ ውድቀት በኋላ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብና የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ወሳኝ የሆነውን የኤሌትሪክ ሃይል በከፍተኛ መጠን ለማምረት ወስኗል። ይህን ተከትሎ አገሪቱ ያላትን እምቅ የኤሌትሪክ የሃይል ምንጭ በመለየት ከፍተኛ ሃይል የማመንጨት ተግባር ተጀመረ። በዚህ መሰረት በውሃ የሃይል ዘርፍ፤ በ1993 ዓ.ም 75 ሜጋ ዋት የሚያመነጨው የጢስ አባይ ማሻሻያ ፕሮጀክት፣ በ1996 ዓ.ም 184 ሜጋ ዋት የሚያመነጨው የጊቤ 1 ሃይል ማመንጫ ፕሮጀክት፣ በ2002 ዓ.ም 310 ሜጋ ዋት የሚያመነጨው የተከዜ ግድብ ፕሮጀክት፣ 2003 ዓ.ም 420 ሜጋ ዋት ሃይል የሚያመነጨው የጊቤ 2 ፕሮጀክት፣ በ2004 ዓ.ም 435 ሺህ ሜጋዋት የሚያመነጨው የጣና በለስ ፕሮጀክት፣ እንዲሁም በያዝነው ዓመት ተመርቆ ወደስራ የገባው 1870 ሜጋ ዋት ሃይል የሚያመነጨው ጊቤ 3 ፕሮጀክቶች ተገነቡ። ከውሃ የሃይል ማመንጫ በተጨማሪ በሃገሪቱ የንፋስ የሃይል ማመንጫዎች ተገንብተዋል። በንፋስ ሃይል ዘርፍ፤ 53 ሜጋ ዋት ሃይል የሚያመነጨው አዳማ 1 ፕሮጀክት፣ 153 ሜጋ ዋት ሃይል የሚያመነጨው አዳማ 2 ፕሮጀክት፣ እንዲሁም 120 ሜጋ ዋት ሃይል የሚያመነጨው አሸንደ ፕሮጀክት ተገንብተው ወደሰራ ገብተዋል። አሁን አጠቃላይ የሃገሪቱ ሃይል የማመንጨት አቅም 4 ሺህ 2 መቶ ሜጋ ዋት ገደማ ደርሷል። ይህ የሃይል መጠን በ1983 ዓ/ም ባሉት 60 አመታት በአጠቃላይ በሃገሪቱ ይመነጭ የነበረውን ሃይል በ12 እጥፍ ያሳደገ ነው። 6 ሺህ ሜጋ ዋት የሚያመነጨውን የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብን ጨምሮ በርካታ የውሃና የንፋስ እንዲሁም የጂኦተረማል የሃይል ማመንጫዎች በመገነባት ላይ እንደሚገኙም ልብ በሉ።

በትራንስፖርት መሰረተ ልማት ዘርፍ ሌላው ትልቅ ግምት የተሰጠውና ድንቅ ክንውንም የታየበት የባቡር ትራንስፖርት ነው። የኢትዮጵያ የባቡር ትራንስፖርት አገልገሎት ታሪክ ከአንድ መቶ ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ነው። ከአዲስ አበባ እስከጅቡቲ የተገነባው የኢትዮ ፈረንሳይ በኋላም የኢትዮ ጂቡቲ የባቡር መስመር፤ ይህ ባለ አንድ ነጠላ ሃዲድ የባቡር መስመር ያረጀና ያፈጀ ነበር። ይህ የባቡር መስመር አገሪቱ አሁን ለተያያዘችውና ላቀደቻው ግዙፍ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ፈጣን እድገት የሚመጣጠን አይደለም። ይህን የኢኮኖሚ እድገትና እንቅስቃሴ የመሸከም አቅም የለውም።

በመሆኑም ሌላ አዲስ ዘመናዊ የባቡር መስመር መዘርጋት ነበረበት። በዚህ መሰረት ከሰበታ/አዲስ አበባ - ሚኤሶ - ደወሌ 656 ኪሎ ሜትር ርዝመት ያለው ባለሁለት ሃዲድ የባቡር መስመር ተገንብቶ ተመርቋል። ከዚህ በተጨማሪ ሌሎች የባቡር መስመር ግንባታዎችም ተጀምረዋል። ግንባታቸውን ለመጀመር በመጠባበቅ ላይ የሚገኙም አሉ። ከመቀሌ እስከ ሃራ ገበያ 268 ኪሎ ሜትር እንዲሁም ከሃራ ገበያ አዋሽ 389 ኪሎ ሜትር የሚሸፍነው ዘመናዊ የባቡር መሰመር ዝርጋታ ተጀምሮ ተጋምሷል። ከሃራ ገበያ አሳይታ 229 ኪሎ ሜትር ከአሳይታ ጅቡቲ ታጁራ ወደብ 210 ኪሎ ሜትር እንዲሁም ከአዲስ አበባ/ሰበታ - ኢጃጂ - ጅማ - ቤዴሌ - ቴፒ - ዲማ 710 ኪሎ ሜትር እንዲሁም ከሞጆ - ሃዋሳ - ወይጦ - ሞያሌ የባቡር መስመር ዲዛይናቸው ተጠናቅቆ ፋይናንስ እየተፈለገላቸው ነው።

ከዚህ በተጨማሪ ወልድያ - ወረታ - ፍኖተ ሰላም 500 ኪሎ ሜትር፣ ወረታ - መተማ 244 ኪሎ ሜትር፤ መቀሌ - ሽሬ 368 ኪሎ ሜትር፤ ኢጃጂ - ኩምሩክ 460 ኪሎ ሜትር፣ ኢተያ - ጊኒር 248 ኪሎ ሜትር የባቡር መስመሮች ግንባታ የዲዛይን ጥናት በመከናወን ላይ ይገኛል።

ከዚህ በተጨማሪ፤ ከህዝብ ቁጥር መጨመርና ገቢው እያደገ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ እጥፍ የጨመረውን የስኳር ፍጆታ (እንደምርት ግብአት ጭምር እያደገ የመጣውን የስኳር ፍላጎት) እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በነበሩት የስኳር ፋብሪካዎች አቅም ማሟላት የማይቻልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በተለይ ከ60 ዓመት በላይ ያገለገለውን የወንጂ ስኳር ፋብሪካ ሙሉ በሙሉ በአዲስ መተካት፤ የተቀሩትንም ነባር ፋብሪካዎች የማሻሻልና የማስፋፊት ስራ ከማከናወን በተጨማሪ አገሪቱ ለስኳር ምርት ያላትን እምቅ አቅም ተከትሎ አዳዲስ የስኳር ፋብሪካዎችን መገንባት አስፈላጊ ነበር።

በዚህ መሰረት በአፋር ተንዳሆ፣ በጣና በለስ፣ በኦሞ ኩራዝ እንዲሁም በወልቃይት የዛሬ 6 ዓመት ገደማ የ10 ግዙፍ ስኳር ፋብሪካዎች ግንባታ ተጀምሯል። እነዚህ ፕሮጀክቶች ከፋብሪካ ግንባታ ባሻገር የመስኖ መሰረተ ለማትም የሚሹ ናቸው። በመሆኑም ግዙፍ ብቻ ሳይሆን ከቴክኒክ አኳያም ውስብስብም ናቸው። የአብዛኞቹ ግንባታ ደግሞ በአገር በቀል ተቋራጮች ነበር የተጀመረው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በዝናብ ላይ ጥገኛ ከሆነ ግብርና አርሶ አደሩን ለማላቀቅ በተለያዩ አካባቢዎች የመስኖና የንጽህ ውሃ አቅርቦት ግድቦች ግንባታ ተጀምሯል።

ከላይ ከብዙ በጥቂቱ ያነሷኋቸው ለአገሪቱ ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገትና ልማት ወሳኝ የሆኑ ግዙፍ ፕሮጀክት ግንባታ ወደኋላ መለስ ብለን ከሃያ አምስት አመታት በፊት ከነበረው ጋር ሲነጻጸር ድንቅና ታሪካዊ ስኬት ነው ማለት ተመዝግቧል ይቻላል። ይሁን እንጂ፤ በብዙ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ላይ የአፈጻጸም ችግር ታይቷል። በተለይ የስኳር ፕሮጀክቶቹና የመስኖ ግድብ ግንባታዎች ላይ ከጊዜ አኳያ ከፍተኛ መጓተት ከወጪም አኳያ ግንባታቸው ሲጀመር ከተያዘላቸው ከእጥፍ በላይ እንዲፈጁ ያደረገ የአፈጻጸም ችግር ታይቷል። ይህ ሁኔታ በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ቅሬታ ፈጥሯል። በመሆኑም ባለፉት ሁለት አመታት የተከናወኑትን የበርካታ ግዙፍ ፕሮጀክቶች ግንባታ ስኬት አደብዝዞት ከአፈጻጸም መጓተትና የወጪ ካለመጠን መጨመር ጋር የተያያዙ ችግሮች ብቻ ጎልተው እንዲታዩ አድርጓል። በግዙፍ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዙሪያ በፍጹም ተገቢ ያልሆኑ የመጓተትና የወጪ መጨመር ችግሮች መኖራቸው ሳይዘነጋ ስኬታማ የነበሩትንም ማሰብ ተገቢ ነው።

ታዲያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በበጀት አመቱ የመንፈቅ አፈጻጸም ዙሪያ ማብራሪያ ለመስጠት በተገኙበት ወቅት በግዙፍ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዙሪያ ስላሉ ችግሮች ከምክር ቤቱ አባላት ጥያቄዎች ቀርበው ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በግዙፍ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ዙሪያ ሚዛናዊ የሆነ ማብራሪያ ነበር የሰጡት፤ ይህ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ በጉዳዩ ዙሪያ ያለውን እውነታ በግልጽ ስለሚያሳይ ልጠቅሰው ወድጃለሁ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ማብራሪያ ሲሰጡ፣ የግንባታ ዘርፍ ለአገሪቱ ገና አዲስ መሆኑን በመግለጽ ነበር የጀመሩት። ከዚህ ጋር ተያይዞ የአመለካከትና የአቅም ችግር መኖሩንም ጠቁመዋል። በግንባታው ዘርፍ የሚስተዋለውን ችግር መቅረፍ ጊዜ ቢፈልግም የዘርፉ ዋነኛ ማነቆ የሆነውን የኪራይ ሰብሳቢነት ችግር ለማስቀረት እየተሰራ መሆኑንም አመልክተዋል።

ከግዙፍ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም መጓተት አለ የሚለውን እየመረረ የመጣ ቅሬታ አስመልክተው በሰጡት ማብራሪያ፣ “ሁሉም ፕሮጀክቶች አልተጓተቱም፤ ሁሉም ግን ጥሩ ሄደዋል ማለት አንችልም” ነበር ያሉት። በአገሪቱ ከተነገቡት ውስጥ ጥሩ አፈጻጸም አላቸው ብለው የባቡር ፕሮጀክቶችን ለአብነት ጠቅሰዋል። የኢትዮ- ጂቡቲ እንዲሁም የአዲስ አበባ ከተማ የቀላል ባቡር በተያዘላቸው ጊዜ ከተጠናቀቁት ውስጥ ይገኛሉ ብለዋል። ከመንገድ ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘም 82 በመቶዎቹ በተያዘላቸው ጊዜ እየተካሄዱ መሆኑንና 18 በመቶዎቹ ላይ ግን መጓተቶች መኖራቸውን ገልጸዋል።

የአውሮፕላን ማረፊያዎች ግንባታዎችም እንደስኬት ማሳያነት ተጠቅሰዋል። የሀዋሳ፣ ሽሬና ጂንካ አውሮፕላን ማረፊያዎች ግንባታ ከተያዘላቸው ጊዜ ቀደም ብሎ መጠናቀቁን የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ሃይለማርያም፣ ግንባታውን ያከናወኑትን የሀገር ወስጥ ተቋራጮች ማመስገን ይገባል ብለዋል። ከሀይል ማመንጫ ጋር ተያይዞም የታላቁ የኢትዮጵያ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በአሁኑ ጊዜ 58 በመቶ ላይ መድረሱን አስታውቀው፣ ግንባታውም በተቀመጠለት የጊዜ ሰሌዳ መሰረት እየተከናወነ መሆኑን ጠቁመዋል።

ከመስኖ ግድቦች እና ከከተሞች የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች ላይ መጓተቶች መኖራቸውን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም፤ “ለፕሮጀክቶቹ ትኩረት መስጠት እንዳለበት ከአፈጻጸማችን ተረድተናል” ብለዋል። በዘርፉ የሚስተዋሉ የአቅምና የልምድ ማነሶችን ለመቅረፍም የውሃ ስራዎች ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት መቋቋሙን ገልጸዋል።

ከስኳር ፋብሪካዎች ጋር በተያያዘም “የስኳር ፕሮጀክቶቻችን ከእቅድ ጀምሮ ችግር እንዳለባቸው መቀበል አለብን” ብለዋል። አስሩን የስኳር ፕሮጀክቶች በአንድ ጊዜ መጀመራቸውን አስታውሰው፣ “ይህ አቅምን የሚፈታተን ነበር” ብለዋል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለጹት ፕሮጀክቶቹ በተጀመሩባቸው አካባቢዎች ምንም አይነት የመሰረተ ልማት ያለመኖሩ አንዱ ችግር ነበር። ያበቃለት ዲዛይን ይዞ ወደስራ አለመግባትና ዲዛይኑን ከግንባታው ሂደት ጋር ለመስራት መወሰኑም ሌላው ችግር ነበር። ያም ሆነ ይህ፤ “በስኳር ፕሮጀክቶቹ ያጋጠሙት ፈተናዎች ከባድ ቢሆኑም አሁን ላይ ግን ታልፈዋል” ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትሩ።

ግንባታውን በሚያከናውኑ ድርጅቶች በኩልም በተለይ የህንድ ኩባንያዎች የአቅም ማነስ እና የባህሪ ችግር እንደነበረባቸው ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል። የተንዳሆ ስኳር ፋብሪካዎችን የሚገነቡት አስራ አንድ ገደማ የህንድ ኩባንያዎች በፕሮጀክቱ መጀመር ማግስት በመሃከላቸው በተፈጠረ አለመግባባት በሃገራቸው ፍርድ ቤት ተካሰው በዚህ ሳቢያ ረጅም ግዜ ስራው መቋረጡ ይታወሳል። በቻይና ኩባንያዎች ግንባታቸው በመከናወን ላይ የሚገኙት ፕሮጀክቶች ግን የተሻለ አፈጻጸም ማሳየታቸውን ነው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተናገሩት።

በአጠቃላይ አገሪቱ ባስመዘገበችው እድገትና በግዙፍ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ድንቅ ስኬቶች ቢመዘገቡም፣ በተለይ ከግዙፍ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም ጋር በተያያዘ በወጉ ያልተሳኩትን ብቻ ሳይሆን የተሳኩትንም ማሰብ ተገቢ ነው። ኢትዮጵያ ለግዙፍ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጀማሪ አገር መሆኗንም ማሰብ ተገቢ ነው። ከፕሮጀክቶች አፈጻጸም ችግር ጋር በተገናኘ አሳሳቢውና ያለምህረት ልንታገለው የሚገባው ኪራይ ሲበሰቢነትን ነው። ለፕሮጀክቶቹ መጓተት ምክንያት የሆኑ የአቅምና የካፒታል እጥረት ችግሮች አገሪቱ ከነበረችበት ሁኔታ የመነጨ በመሆኑ ከእድገታችን ጋር እየኮሰሰ የሚሄድ ነው። እናም ስለ ግዙፍ ፕሮጀክቶቻችን ስናስብ ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንደገለጹት “ሁሉም ፕሮጀክቶች አልተጓተቱም፤ ሁሉም ግን ጥሩ ሄደዋል ማለት አንችልም” ። እናም በጥሩ ከተከናወኑት የተገኘውን ልምድ፣ ችግር በገጠማቸው ላይ በመጠቀም በሂደት ምሉዕ መሆኑን እናስብ!